# ምዕራፍ አምስት

## መስማት የተሳናቸው ባህል መገለጫ ባሕርያት




ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች


ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣

» ከመስማት የተሳናቸው ባህል ጋር የተያያዙ ምልክቶችእውቀታችሁን ታዳብራላችሁ፣
» የመስማት የተሳናቸው ባህል መገለጫ የሆኑትን ነጥቦች በኢምቋታስረዳላችሁ፣
» ከምንባቡ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን ትለያላችሁ፣
» ከቁልፍ ምልክቶች ውስጥ በሁለት እጅና በአንድ እጅ የሚሰሩ ምልክቶችን ታሳያላችሁ፣
» የኢምቋ ዐረፍተ ነገር ትሰራላችሁ፣
» የምልክቶችን ክፍሎች ትተነትናላችሁ፣
» ስርዓት ጠብቃችሁ ትወያያላችሁ፣
» በኢምቋ ናሙና ሰዋሰው ውስጥ ያሉትን ተሳቢዎች ታስረደላችሁ።


## ቁልፍ ምልክቶች




የጋራ ህይወት




መንገድ




ቴሌቪዥን




ሥነምግባር




እምነት




አካል ጉዳት





አቋም




ውበት


አመለካከት



ኪነጥበብ



ደንብ


ታሪክ



ክበብ



ሰዓሊ


ተቋም


አናሳ ቋንቋ


እውቅና


ምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ



ማህበረሰብ



መስማት የተሳናቸው ባህል

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### እይታዊ ንባብ



1. ከላይ የተቀመጡትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ተመልክተችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ

አስረዱ::

2. በስዕሎች ላይ ከተቀመጡት ነገሮች ጎልቶና ገዝፎ የሚታየው ምንድን ነው?

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ በኢምቋ ያቀረቡላችኋል:: መምህራችሁን በጥንቃቄ ተከታትላችሁ ለጥያቄዎች በኢምቋ መልስ ስጡ::

1. መስማት የተሳናቸው ባህል መኖሩን የምንረዳው በምን መንገድ ነው?
2. በመስማት የተሳናቸው ባህል ውስጥ የሚታቀፉ ሰዎች እና ተቋማት እነማን ናቸው?

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

### ምንባብ

ተማሪዎች፤ መምህራችሁ መስማት የተሳናቸው ባህል መገለጫ ባሕርያት የሚለውን ምንባብ ሲያቀርቡላችሁ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን፣ የኢምቋ አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ::

### መስማት የተሳናቸው ባህል መገለጫ ባሕርያት

ብዙዎቹ ለመስማት የተሳናቸው ባህል የተሰጡ ትርጉሞች የሚያሳዩት፣ የመስማት የተሳናቸው ባህል የመስማት የተሳናቸው የጋራ የህይወት መንገድ፣ እምነት፣ አቋም፣ አመለካከት፣ ኪነ ጥበብ፣ ታሪክ፣ እሴቶችና ተቋማት መሆናቸውን ነው:: እነዚህን መገለጫዎች አንድ በአንድ ማየት ስለመስማት የተሳናቸው ባህል የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖረን ይረዳል::

የመስማት የተሳናቸው እሴቶች የሚባሉት የምልክት ቋንቋ ውበትና እድገት፣ የመስማት የተሳናቸው ማሰባሰብ፣ ትምህርት በምልክት ቋንቋ፣ በአስተርጓሚ የሚሰጡ አገልግሎቶች፣ የአስተርጓሚዎች የሙያ ብቃት፣ መንግሥት የሚሰጠው እውቀትና፣ በምልክት ቋንቋ የሚቀርቡ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ የመስማት የተሳናቸው ማህበረሰብ ታሪክ፣ ወዘተ ናቸው::

የሚማሩባቸው መንገዶች ደግሞ በምልክት ቋንቋ የመግባባት ባሕርይ፣ ሲደሰቱ፣ ሲያዝኑ፣ ሲናደዱ፣ ወዘተ፣ ስሜታቸውን በምልክት ቋንቋ መግለጽ መቻል ናቸው:: እንዲሁም የአድማጩን ትኩረት ለመሳብ በዕይታ ክልል ውስጥ እጅ ወይም ጎላ ብሎ ሊታይ የሚችል ነገር ማርገብገብ፣ ትክሻን በቀስታ መጠብጠብ፣ ወለል ወይም ጠረጴዛን በቀስታ

መተምተም፣ መብራት ብልጭ ድርግም ማድረግ፣ በቅርብ ያለውን ሰው የአድማጬን ትኩረት ለመሳብ እንዲረዳ መጠየቅ የሚጠቅሙ ናቸው::

ሌላው በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸውን የህይወት መንገድ ይመለከታል:: ለምሳሌ ፊት ለፊት እጆችና ፊት በግልጽ በሚታይበት ሁኔታ መናገር የግድ ነው:: ከመስማት የተሳነው ሰው ጋር ሲገናኙ አለመስማትነትንና ራስን ማስተዋወቅ የጥሩ ስነ ምግባር ምልክት ነው:: እንዲሁም ከመስማት የተሳናቸው ጋር ሲገናኙ ሁሉንም ሰላም ማለትና ሲለያዩም ሁሉም እንዲያውቁ ማድረግ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አለው::

አመለካከትን በሚመለከት ደግሞ አለመስማትን እንደ አካል ጉዳት ሳይሆን እንደ መለያ መመልከት ነው:: የመስማት የተሳናቸው ማህበረሰብ ራሱን የራሱ ቋንቋና ባህል ያለው አናሳ ማህበረሰብ አድርጎ ያያል:: ይህም ማህበረሰቡ በባህሉና በቋንቋው የሚኮራ እንጅ የሚሸማቀቅ አይደለም::

በማህበረቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ልማዶች የምንላቸው የምልክት ስም መስጠት፣ በቂ ብርሃን ባለበት ቦታ መሰብሰብ፣ የጋራ የመገናኛ መድረኮች መፍጠር፣ ግልጽነት፣ ስለ ሌሎች የግል ህይወት ብዙ መጠየቅ፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ነው::

የመስማት የተሳናቸው ማህበረሰብ ተቋማት የምንላቸውና የባህላቸው አካል የሆኑት የመስማት የተሳናቸው ማህበራት፣ የመስማት የተሳናቸው ት/ቤቶች፣ የመስማት የተሳናቸው የእምነት ተቋማት፣ የመስማት የተሳናቸው ክበቦች፣ የመስማት የተሳናቸው የቴያትር፣ የዘፈን፣ የዳንስ፣ የዝማሬ ቡድኖች፣ ወዘተ ናቸው::

ኪነጥበብ በመስማት የተሳናቸው ባህል ውስጥ በምልክት ቋንቋ የተዘጋጁ ዘፈኖችና ቴአትሮች፣ መስማት የተሳናቸው ደራሲያን ወይም ሰዓሊያን ስራዎች፣ መስማት በተሳናቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ መጽሔቶች ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው::

በመጨረሻም መስማት የተሳናቸው ታሪክ የምንለው ነው:: ይህም የምልክት ቋንቋ ታሪክ፣ የመስማት የተሳናቸው ተቋማት ታሪክ፣ የታዋቂ መስማት የተሳናቸው ግለሰቦች ታሪክ፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል::

*ምንጭ:- ጳውሎስ፣ 2007 የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ማስተማሪያ መመሪያ፣ (ተሻሽሎ የቀረበ)*

## መልመጃ አንድ:-

### አይቶ መረዳት

የሚከተሉት ጥያቄዎች በዋናነት በምንባቡ ውስጥ የተማራችኋቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶችና ዐረፍተ ነገሮች አጠቃቀም ግንዛቤያችሁን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ::

1. ከምንባቡ ውስጥ የወደዳችሁትን አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ መምህሩ ባቀረቡበት መንገድ በክፍል ውስጥ በኢምቋ አንብቡ፡፡
2. የምንባቡ ዋና ዋና ነጥቦች ጥቀሱ፡፡
3. የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍል ውስጥ አስረዱ፡፡

## መልመጃ ሁለት፡-

### የማስታወስ ችሎታ

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ  በኢምቋ መልሱ፡፡

1. በምንባቡ መሰረት የመስማት የተሳናቸው ባህል እሴቶች የምንላቸው የትኞቹ ናቸው?
2. በመስማት የተሳናቸው ባህል ውስጥ መግባባት የሚቻለው እንዴት ነው?
3. በመስማት የተሳናቸው ባህል ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ስነ ምግባሮች ምን ምን ናቸው?
4. በመስማት የተሳናቸው ባህል ዘንድ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?
5. በመስማት የተሳናቸው ባህል ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ልማዶች ምን ምን ናቸው?
6. በመስማት ተሳናቸው ባህል ዘንድ ተቋማት የምንላቸው የትኞቹን ነው?
7. በመስማት የተሳናቸው ባህል ዘንድ ኪነ ጥበብ እንዴት ይገለፃል?
8. በመስማት የተሳናቸው ባህል ዘንድ ታሪክ የምንላቸውነገሮች ምን ምን ናቸው?

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## የቡድን ስራ

## መልመጃ አንድ፡-

### በቡድን መስራት

መምህራችሁ በቡድን ይከፋፍሏችኋል፡፡ በቡድን ከተከፋፈላችሁ በኋላ መስማት የተሳናቸው ባህል ከሌሎች ባህሎች በምን በምን ሁኔታዎች እንደሚለይ ተወየዩ፡፡ የውይይታችሁን ውጤት በቡድናችሁ ተወካይ በኩል ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ አቅርቡ፡፡

## መልመጃ ሁለት፡-

### ዐረፍተ ነገር ምስረታ

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው፡፡ በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች በመጠቀም የራሳችሁን የኢምቋ ዐረፍተነገር ስሩ፡፡

1. እውቅና
2. ቴሌቪዥን
3. ሰላምታ
4. አድራሻ
5. መተዋወቅ
6. ስነ ምግባር
7. ህይወት
8. ግልጽነት
9. እምነት
10. ሰዓሊ
11. መጽሔት
12. ታሪክ

## መልመጃ ሦስት፡-

### በሁለትና በአንድ እጅ የሚሰሩ ምልክቶች

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶች ወክለው የተቀመጡ ናቸው፡፡ በቃላቱ ከተወከሉት ምልክቶች መካከል በሁለት እጅ የሚሰሩትንና በአንድ እጅ የሚሰሩትን ለይታችሁ በክፍል ውስጥ ዓሣዩ፡፡

ምሳሌ፡-

ኢትዮጵያ፡ በአንድ እጅ የሚሰራ ምልክት

ማኅበረሰብ: በሁለት እጅ የሚሰራ ምልክት

1. አስተርጓሚ
2. መንግሥት
3. መደሰት
4. መረጃ
5. ሰው
6. መጠየቅ
7. ጉዳይ
8. ባህሪ
9. ልዩ
10. ግን
11. ጥሩ
12. መጥፎ
13. ህይወት
14. እምነት
15 መጽሔት
16. መፍጠር
17. መኩራት
18. ስራ
19. ድምጽ
20. በቂ

## ክፍለ ትምህርት አራት

### የምልክት ትንታኔ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችኋቸውን ዋና ዋና ምልክቶች ትንተና በክፍል ውስጥ ዓሣዩ::

ምሳሌ:- ብልጭ

1. የእጅ ቅርጽ:- የተዘረጉ እጆች
2. የእጅ ቅርጽ የሚያርፍበት ቦታ:- ከደረት ፊት ለፊት
3. የመዳፍ አቅጣጫ:- ወደታች
4. የእጅ እንቅስቃሴ:- ከላይ ወደታች
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች:- የፈጠጠ አይን

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## የኢምቋ ሰዋስው ተሳቢዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን የኢምቋ ሰዋሰው ናሙናዎችን በጥንቃቄ አጥንታችሁ ከናሙናዎቹ ቀጥሎ የተሰጠውን መልመጃ ስሩ።

1. አማርኛ፡- ከበደ ደብተሬን ወሰደብኝ።

   ኢምቋ፡- ከበደ ወሰደ ደብተር።

2. አማርኛ፡- መኪናው ቤቱን ገጨው።

   ኢምቋ፡- መኪና ገጨ ቤት።

3. አማርኛ፡- አስተማሪው ፈተናዬን አረመው።

   ኢምቋ፡- አስተማሪ ማረም ፈተና።

4. አማርኛ፡- ሃኪሙ ልጁን መረመራት።

   ኢምቋ፡- ሃኪም መረመረ ልጅ።

5. አማርኛ፡- በሬው ሳሩን ይግጣል።

   ኢምቋ፡- በሬ መጋጥ ሳር።

ተሳቢ ማለት ድርጊቱ የተፈፀመበት ሰው ወይም እንስሳ ወይም ዕቃ ማለት ነው።

በቡድን በመሆን ከላይ በቀረበው የኢምቋ ናሙና ሰዋሰው ተሳቢዎችን ለመምህራችሁ ዓሣዩ።